
# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ የአድነት ንቅናቄ

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ የአንድነት ንቅናቄ በሚል ርእስ ለመጻፍ በምንነሣሣበት ጊዜ ከቅድመ ክርስትና በፊት ያለውን አንድ ከፍተኛ ነጥብ ከዚህ ላይ መጥቀሱ ተገቢ ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ቀጥሎ ሁለተኛ ክብር የሚሰጠው ክብረ ነገሥት እንደሚናገረው የንግሥተ ሳባ ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም መሄድና ከንጉሥ ሰሎሞን ጋር መገናኘት፤ በልጅዋም በቀዳማዊ ምኒልክ አማካይነት የታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት፤ በክርስትናው ሃይማኖትም ዘንድ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን አምሳልና መርገፍ፤ ሰምና ወርቅ ሁነው የሚኖሩበት ቤተ ክርስቲያንና ሀገር ቢኖር ኢትዮጵያ ብቻ ስለሆነች፤ ከቅድመ ክርስትና በፊት ይህን የመሰለ ግንኙነት ነበር ብሎ ታሪክን ከታሪክ ጋር ማገናኘት ተገቢ ነው። እንግዲህ የያዝነው ርእስ ከድኅረ ክርስትና በኋላ ያለውን የሚያስተነትን ስለሆነ ወደ እርሱ እንመለሳለን።




የቤተክርስቲያን ዓለም አቀ ፋዊ ግንኙነት ከዚያው ከአንደኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስካሁን ሳያቋርጥ የኖረ ነው ማለት ይቻላል። ዋና ዋና የሆነውን የታሪክ ምዕራፍም እንደ ሚከተ ለውሁኖ እናገኘዋለን። በ፴፬ ዓ.ም. ላይ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሳለም የሄደው የኢትዮጵያ ንግ ሥት ገንዘብ ያዥ የነበረው ጃንደረባ የክር ስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ አድርጓል። ከዚያም አባ ሰላማ ተብሎ የሚጠ ራው የቅዱስ ፍሬምናጦስና የዘጠኙ ቅዱሳን ወኢትደዮጵያ መግባት ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር መሠረት ጥሏል። በተለይም በ፲፩ኛው ክፍለ ዘመን በንጉሥ ላሊበላ ጊዜ ብዙ የውጭ ተወላጆች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ ግንኙነት እንዲኖር ሙከራ አድርገዋል። እንዲሁም በ፲፫ኛውና ፲፬ኛው ክፍላተ ዘመን የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የበኔዲክት መነኮሳት እስከ ደብረ ዳሞ ደረስ በመሄድ ክርስቲያናዊ ግንኙነት እንዲኖር ጥረት አድርገው ነበር። በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን በግራኝ መሐመድ ወረራ ጊዜም ዓለም አቀፋዊው የክርስትና ሃይማኖት ግንኙነት እንዲስፋፋ ብዙ ጥረት ተደርጎ ነበር። ይሁን እንጅ የተጀመረው ክርስቲያናዊው ዓለም አቀፍ ግንኙነት በተመጣጣኝ ደረጃ ወይም አቻ ላቻ ሊካሄድ አልቻለም። ኢየሱሳውያን የተባሉ ሚሲዮናውያን የነበረውን መልካም ግንኙነት አዛቡት። እንዲያውም በ፲፮ኛው ክፍለ ዘመን ለ፴ ዓመት የእርስ በእርስ ጦርነት ያለ አግባብ ተካሂዶ ብዙ ሕዝብ አለቀ። መጻሕፍት ተቃጠሉ፤ ገዳማትና አድባራት ተመዘበሩ። ኢየሱሳውያንም ከኢትዮጵያ እንዲባረሩ ተደረገ። እነርሱም ከተባረሩ በኋላ አላዛራውያን፤ ቡናማ ቀሚስ ለባሾች (ካፑሲናውያን) የሚባሉ የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሚሲዮናውያን በመግባታቸው የውስጥ ሰላም ሊገኝ አልተቻለም። የውጭ ሚሲዮናውያን በአመጡት የሃይማኖት ልዩነት የቅባት፤ የጸጋና የተዋሕዶ ክርክር መነሣት የጎንደርን ሥርወ መንግሥት አዳከሞ፤ የእርስ በእርስ ሽኩቻ የሞላበት ዘመነ መሳፍንት እንዲመጣ አረገ። አሁን እንደሚታየው የዞንና የክልል ክፍፍል ማለት ነው። ሁሉም በያለበት ራስ ወዳድ በመሆኑ ማዕከላዊው አስተዳደር ተገርስሶ ወደቀ። የራሷ የሆነ ርእሰ ቤተ ክርስቲያን የሌላት ቤተ ክርስቲያንም መልሕቅ እንደሌለው መርከብ ከወዲያ ወዲህ ተቀዘፈች። ሆኖም በአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በ፲፰፻፸ ዓ. ም. በግንቦት ወር በቦሩ ሜዳ በተደረገው ጉባኤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አንድነት እንደገና ተመሠረተ።

ከላይ የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሚሲዮናውያን ለዓለም አቀፋዊው ግንኙነት አለመጠናከር ምክንያት እንደሆኑ ተገልጿል። በእነርሱም አንጻር የስካንድኒቭያን፤ የምዕራብ አውሮፓና የሰሜን የአሜሪካ ፕሮቴስታንቶች ሚሲዮናውያንም በአፍሪካ ክፍለ ዓለም ያለችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በማጠናከር ፈንታ በተሐድሶ ስም ዓለም አቀፋዊው ክርስቲያናዊ ግንኙነት ሊጠነክር አልቻለም። ስማቸው እንደሚያመለክተው በመለያየት ላይ መለያየትን፤ በተቃውሞ ላይ ተቃውሞን እየፈጠሩ ከእናት ቤተ ክርስቲያናችን ጋር ባለመስማማታቸው አለመተማን፤ የጎሪጥ መተያየትና የእርስ በእርስ ጥላቻ ሥር እየሰደዱ እንዲኖሩ ሁኗል። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኀበር ከተመሠረተ በኋላ ያለውን ታሪካዊ ሂደት እንድሚከተለው መመልከት ይቻላል።

*<u>ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ ንቅናቄ</u>*

በጀርመንኛ ቋንቋ Oekumene- *ኢኩሜኔ* እየተባለ የሚነገረውና በየጊዜው የምንሰማው ቃል በግሪከኛው Oikos- *ኦኢኮስ* የሚለው ነው። ትርጓሜውም በአጠቃላይ ሰው የሚኖርበት የምድር ዙሪያ፣ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ፣ ከአድማስ እስከ አድማስ እንደማለት ሲሆን <u>በዓለሙ ሁሉ</u> ለማለት ነው። ከዚህም ላይ ለማስረጃ ያህል በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ ፪ በቁጥር ፩ ላይ ያለውን ስንመለከት „ *በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዛ ወጣች፡፡* “ ይላል። ይህም የተነገረው የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ጊዜ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረው ቃል „ *እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ* ከእናንተ ጋር *ነኝ፡፡*“ የሚል ነው። ሜቴ.፳፰፣ ፳። በሐዋርያት ሥራ ደግሞ „ *እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ፡፡* “ ይላል። (፩፣፰) „ *እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ* „ እና „ *እስከ ምድር ዳርም ድረስ* “ የሚለው ተወራራሽ ሰለ ሆነ ማብራራት አስፈላጊ አይመስልም። በመጨረሻም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፍርድ ዳግመኛ ከመምጣቱ በፊት ስለሚታየው ምልክት ሲናገር „ *ለአሕዛብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፡፡* “ ብሏል። ማቴ.፳፬፣፲፬። እስካሁን የተመለከትነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን፣ በዓለም ላይና በምድር ዙሪያ የተፈጸመውንና ወደፊትም የሚፈጸመውን ነበር።

የክርስትና ሃይማኖት በኢየሱስ ክርስቶስ ተመሥርቶ ወደ ሐዋርያት፣ ከሐዋርያት ወደ ሰብዓ አርድእት፣ ከሰብዓ አርድእት ወደ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ተላለፈ። በዘመናት መካከል ደግሞ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ከመዓዝን እስከ መዓዝን ተዳረሰ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደተመዘገበው በሦስቱ ክፍላተ ዓለማት አምስት መናብረተ ሊቃነ ጳጳሳት ተመሠረቱ። ለአምስት መቶ ዓመታትም ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ ጉባኤን በማካሄድ፣ ሲኖዶሳዊ ውሳኔን በማሳለፍ የቤተ ክርስቲያን ኅብረት እጅግ የጠነከረ ነበር፡፣ በ፬፻፶፩ (451) ዓ. ም. ላይ ግን ቤተ ክርስቲያን ከሁለት ተከፈለች። የሸውም የካልቄዶን ጉባኤ በመባል የሚታወቀው ነው። ሮምና ቁስጥንጥንያ በአንድ ወገን ሲሰለፉ፣ አንጾኪያና እስክንድርያ ደግሞ አንድ ግንባር ፈጠሩ። የኢየሩሳሌሙ መንበረ ሊቀ ጵጵስና ግን ሚዛን ወደ አጋደለበት ጠጋ ሲል ኖረ። ከዕለት ወደ ዕለት መለያየቱ እየሰፋ ሲሄድ የቁስጥንጥንያው ፓትርያርክ የዓለም ፓትርያርክ እኔ ነኝ ብሎ ተነሣ። የሮሙም ፓፓ እያንገራገረ እስከ ፲፩ኛው ክፍለ ዘመን አንድ ግንባር ፈጥረው ኖሩ። በ፲፻፶፬ (1054) ዓ. ም. ግን እርስ በእርሰ ተወጋግዘው ተለያዩ። ከጊዜ ወደ ጊዜ የአረቦችና የቱርኮች ኃይል እያየለ ሲሄድ ታላቁ የቢዛንታይን መንግሥት ተዳከመ። በመጨረሻም መናገሻ ከተማው ቁስጥንጥንያ (እስታንቡል) በቱርኮች እጅ ወደቀ። በአሁኑ ጊዜ በእስታንቡል ከ ፪ሺህ እስከ ከ፬ ሺህ የሚገመቱ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ይገኛሉ። አሁንም ፓትርያርካቸው የዓለም ፓትርያርክ የሚለውን የመጨረሻውን የመዓርግ ስም እንደያዘ ይገኛል። ከዚህ ላይ ወደ ቁስጥንጥንያው መንበረ ፓትርያርክ ታሪክ ውስጥ የገባነው የተነሣንበት ርእስ ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ ንቅናቄ የሚል ስለሆነ የቁስጥንጥንያው መንበረ ፓትርያርክም „ የዓለም ፓትርያርክ “ የሚለውን መጠሪያ ያወጣው ዓለም አቀፋዊነቱን ለማረጋገጥ እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው።

የፕሮቴስታንት ሃይማኖት መሥራች የሆኑት ማርቲን ሉተርና ዮሐንስ ካልቪን ከመነሣታቸው በፊት የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በአውሮፓ ክርስቲያኖች ዘንድ ክፍተኛ ሚና ተጫውታለች። በእርሷም መሪነት ነበር ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን ከእስላሞች ነጻ ለማውጣት የመስቀል ጦርነት የተካሄደው። በዚህም ጊዜ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን በቁጥጥር ሥር ለማድረግ ብዙ ሙከራ ተደርጓል። ሆኖም ውጤት አልተገኘበትም። እንዲያውም የበለጠ አለመተማመን ሥር እየሰደደ፣ ጥላቻ እየሰፋ ሄደ። ይሁን እንጅ በ፲፬፻፴፱ (1439) ዓ. ም. የምሥራቅና የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት አባቶች የተካፈሉበት ዓለም አቀፍ ስብሰባ በፍሎሬንስ ከተማ ተካሄደ። ዓላማውም የተከፋፈሉትን አብያተ ክርስቲያናት መልሶ ለማዋሐድ ነበር። በዚህም ታላቅ ዓለም አቀፍ ስብሰባ ላይ በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ተወክለው በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት አስተዳዳሪ አባ ኒቆዲሞስ የተባሉ ቆሞስ ከአንድ ዲያቆን ጋር ተገኝተዋል። የተጠበቀው የአብያተ ክርስቲያናት አንድነት ግን አልተገኘም። የፍሎሬንሱ ስብሰባ ከተካሄደ ከ፩፻ ዓመት በኋላ በምዕራብና በሰሜን አውሮፓ ብቸኛ የነበረችው የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በፕሮቴስታንቶች ኃይል ተናጠች። ፓፓዋም ተነቀፈ። የፕሮቴስታንት ሃይማኖት መሥራች የሆነው ማርቲን ሉተር „ *ማንኛውም ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን እንደፈለገ መተርጎም ይችላል* „ የሚል መመሪያ በመስጠቱ ከእርሱ በኋላ የተነሡ ተከታዮቹ ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ዓረፍተ ነገር እየመዘዙ እንደ ባቢሎናውያን እርስ በእርስ ተለያዩ። በአሁኑ ጊዜ በሺህ የሚቆጠሩ የሃይማኖት ልዩነት ያላቸው የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ። አብዛኞቹ በበለጸጉት ሀገሮች ዘንድ ስለሚገኙ የበረከቱ ተቋዳሾች ሁነዋል። ከዚህም በመነሣት የብሱን በባቡርና በመኪና፣ ባሕሩን በመርከብ፣ ሰማዩን በአይሮፕላን በማቋረጥ ያልደረሱብት ቦታ የለም። ሚሲዮናውያን በቅኝ ገዥዎች አማካይነት በእስያ፣ በአፍሪካ፣ በላቲን አሜሪካና በውቅያኖስ ደሴቶች ባሉ ሀገሮች ላይ በማስተማራቸው አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ተቋቋሙ። ወንጌልን ማዳረሳቸው መልካም ሁኖ ሳለ፣ እርስ በእርሳቸው በፍቅር የሚተያዩ ሁነው አለተገኙም። አንዱ ያንዱን መንጋ መንጠቅ ጀመረ። ይህን ሕገ ወጥ ተግባር ለማስቆም፣ በ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን ኅብረትን የሚያሳዩ ድርጅቶች አየተስፋፉ ሄዱ። አንዳንዶቹን ከዚህ ላይ መመልከት ይቻላል። የዓለም ክርስቲያኖኞች፣ የዓለም ክርስቲያናውያን ወጣቶች፣ የዓለም ክርስቲያናውያት ሴቶች፣ የዓለም ሚሲዮኖች፣ የዓለም ወንጌላውያን፣ የዓለም ክርስ ቴያኖኞቿ ተማሪዎች ወዘተ የሚሉ ናቸው። አሁን መቀመጫውን ጀኔቫ ላይ ያደረገው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ከመመሥረቱ በፊት በ፳ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ክርስቲያናዊ የሆነ ዓለም አቀፍ ስብሰባ ተካሄደ። „ *ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ ንቅናቄ* “ ም ተብሎ ተጠራ። ዋና መሪ ሀሳቡም „ *ዓለም አቀፋዊ አንድነት በክርስቶስ* “ የሚል ነበር። ዓለም አቀፍ የሆነውን ክርስቲያናዊ ንቅናቄ ለመፍጠር ጽንስ ሀሳቡ የፈለቀው ስለ ዓለም ድኅነት ሲል የተወለደውንና የተሰቀለውን ብሎም በድል አድራጊነት የተነሣው ኢየሱስ ክርስቶስን በጋራ ለመስበክ ነው። ለዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ ንቅናቄ መሠረት ሁኖ የሚጠቀሰው በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ ፫ በቁጥር ፲፮-፲፰ ያለው „ *በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና፡፡ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጅ፣ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አላከውምና፡፡ በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፣ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል፡፡* “ የሚለው መለኮታዊ ቃል ነው። ይህም ገጸ ምንባብ „ *ትንሹ ወንጌል* “ በመባል ይታወቃል።

በአውሮፓ የአንደኛው የዓለም ጦርነት እንዳበቃ የማርክሳውያንና የሌኒናውያን አምላክ ቢስነት ምሥራቅ አውሮፓን አጥለቀለቀው። የኮሚኒስቱም ሥርዓት ከምሥራቅ አውሮፓ አልፎ ወደ ሌላው ክፍለ ዓለም ተዛመተ። በክርስቲያኖች ዘንድ ዓለም አቀፍ ኅብረት መፍጠሩ አስፈላጊ ሁኖ ተገኘ። እንደመመሪያም ሁነው ከተያዙት ዓበይት አናቅጽ ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል። <u>፩ኛ አንድነት፣ ፪ኛ</u> <u>ምስክርነት፣ ፫ኛ አገልግሎት</u> የሚሉ ናቸው።

በተለይም ለብዙ መቶ ዓመታት ወደተውት ወደ ጸሎተ ሃይማኖት ቀኖና ተመልሰው „ *ከሁሉ በላይ (ካቶሊካዊት) በሆነች ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን፡* “ በማለት አቋማቸውን ለማስተካከል ፈለጉ። በ፲፱፻፲፯ (እ.አ.አ. 1925) ዓ. ም. ላይ በስቶክሆልም ከተማ በተደረገው የዓለም ሚሲዮናኞች ስብሰባ ላይ „ አንድነት “ በሚለው መርሐ ግብር ለመስማማት ባይቻልም „ ምስክርነትና አገልግሎት „ በተባሉት ላይ ግን መስማማት ተችሏል። በዚህም ስብሰባ
„ *በክርስቶስ ኃይል ለመታረቅ ችለናል፤*“ ሲሉ መግለጫ አወጡ።

*<u>የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር</u>*

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ከመቋቋሙ በፊት የዓለም አቀፍ ሚሲዮን ምክር ቤት፤ የእምነትና የሥርዓት ንቅናቄ የሚባሉ ድርጅቶች ነበሩ። እነዚህም ድርጅቶች ወደ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርነት እንዲለወጡ ተከታታይ ስብሰባዎች ተካሄዱ። የአንደኛው ዓለም ጦርነት በ፲፱፻፲ ( እ.አ.አ. 1918 ) ዓ. ም. በመነሣቱ ብዙም ለመሥራት አልተቻለም። ቀጥሎም በሁለተኛው ዓለም ጦርነት በ፲፱፻፴፫ ( እ.አ.አ. 1941 ) ዓ. ም. በመካሄዱ አንደኛውን ተጻፈነ። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር እንዲቋቋም ግንባር ቀደም የሆኑት ሕዝቦችና ሀገሮች በጦርነት ውስጥ ተማገዱ። ሆኖም ጦርነቱ ከአበቃ በኋላ በ፲፱፻፵ ( እ.አ.አ. 1948 ) ዓ. ም በወርኃ ነሐሴ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በአምስተርዳም ከተማ ተቋቋመ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚያን ጊዜ የሐረር ጠቅላይ ግዛት ሊቀ ጳጳስ በኋላም የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በነበሩት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አማካይነት መሥራች አባል ለመሆን በቃች። እንዲሁም የግብጽ፤ የሶርያ፤ የህንድና የግሪክ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሥራች አባል ሁነዋል። የሩስያና የሌሎቹም የምሥራቅ አውሮፓ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ግን በነበረው የኮምኒስት ተጽእኖ መልእክተኞቻቸውን ለመላክ አልቻሉም። የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ሊቃውንት በጉባኤው ላይ ለመገኘት ፈቃደኞች ነበሩ። ነገር ግን ፓፓው ፒዩስ ስለከለከላቸው በጉባኤው ላይ ሳይሳተፉ ቀሩ።

የጉባኤው ዋና መሪ ሀሳብ „ *የሰው ልጅ ሕገ ወጥነትና የእግዚአብሔር ዕቅድ* “ የሚል ነበር። ከዚህም ሌላ „ *በአንድ ላይ ተባብረን ለመኖር እንሻለን* “ የሚል ውሳኔ ተላልፏል። በዚህ ጉባኤ ላይ አያሌ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል። ጦርነት የሚያስከትለው እልቂት ከፍተኛ በመሆኑ „*ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ውጭ ነው*“ በሚል ተወግዟል። „*ምእመናን የቤተ ክርስቲያን አካል ስለሆኑ ተገቢ ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል*“ የሚልም ይገኝበታል። በተለይም እርስ በእርስ ለመረዳዳት የሚያስችል መመሪያ ተሰጥቷል። አጠቃላይ ጉባኤው በየ፯ ዓመቱ እንዲደረግ ተወስኗል። በዚህ ጉባኤ ላይ ከ፩፻፵፯ አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ ፫፻፶፩ መልእክተኞች ተካፋዮች ሁነዋል።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አባል ለመሆን እነዚህን ፫ መመሪያዎች አምኖ መቀበል ግዴታ ነው። <u>፩ኛ በቅድስት ሥላሴ በአብ፤ በወልድ፤ በመንፈስ ቅዱስ ስም በአንድ አምላክ አምኖ መጠመቅ፤ ፪ኛ ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ልጅና የዓለም አዳኝ አድርጎ ማመን፤ ፫ኛ ቅዱሳት መጻሕፍትን አምላካውያት መጻሕፍት አድርጎ መቀበል</u> የሚሉ ናቸው። በዚህ በአምስተርዳሙ ጉባኤ የማኅበሩ የመተዳደሪያ ደንብ እንዲጸድቅ ተደርጓል። መቀመጫውም ጀኔቫ ላይ እንዲሆን ተወስኗል። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ሁለት ሕጋውያን አካሎች አሉት። ፩ኛው በየ፯ ዓመቱ የሚደረገው አጠቃላይ ጉባኤ ሲሆን ፪ኛው ደግሞ በአጠቃላይ ጉባኤው የሚመረጠው ማዕከላዊ ኮሚቴ ነው። የማኅበሩ ምክር ቤት በ፮ ፕሬዚደንቶችና በአንድ ጠቅላይ ጸሐፊ የሚመራ ሲሆን በውስጡም የተለያዩ መምሪያዎች አሉት።

፪ኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጉባኤ በ፲፱፻፵፮ ( እ.አ.አ.1954 ) ዓ. ም. በሰሜን አሜሪካ ኢቫንስተን በተባለ ከተማ ተካሄደ። በዚህም ጉባኤ ከ፩፻፷፩ አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ ፭፻፪ መልእክተኞች ተካፋዮች ሁነዋል። የጉባኤው መሪ ሀሳብ „ *ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ተስፋ ነው፡* “ የሚል ነበር። እንደዚህ ያለው መሪ ሀሳብ በትላልቅና በዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ዘንድ የተለመደ መፈክር ስለሆነ ወደፊትም በየጉባኤው የተለያዩ መሪ ሀሳቦችን እንመለከታለን። አሁንም በዚህ በ፪ኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጉባኤ የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞቿን አላከችም። ሆኖም በ፲፱፻፶፪ ( እ.አ.አ.1960 ) ዓ. ም. በስኮትላንድ ሴንት አንድርዩስ በተባለ ከተማ በተደረገው የዓለም፤ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ንዑስ ክፍል በሆነው የእምነትና የሥርዓት ሰብሰባ ላይ መልእክተኞቿን ልካለች።

፫ኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጉባኤ በ፲፱፻፶፫ ( እ.አ.አ.1961 ) ዓ. ም. በኒውደልሂ ተካሄደ። በዚህም ጊዜ የምሥራቅ አውሮፓ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አባላት ሁነዋል። ከ፩፻፺፯ አብያተ ክርስቲያናት የትላኩ ፭፻፸፯ (577) መልእክተኞች በጉባኤው ተካፋዮች ሁነዋል። የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንም ለመጀመሪያ ጊዜ ፭ መልእክተኞችን ልካለች። የጉባኤው መሪ ሀሳብ „ *ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ብርሃን ነው፡*“ የሚል ነበር።

፬ኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጉባኤ በ፲፱፻፷ ( እ.አ.አ.1968 ) ዓ. ም. ኡፕሳላ ውስጥ ተካሄደ። በጉባኤው ከ፪፻፴፭ አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ ፯፻፬ ( 704 ) መልእክተኞች ተገኝተዋል። አባል ካልሆነችው ከሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንም የተላኩ ፲፬ መልእክተኞች ተካፋዮች ሁነዋል። የጉባኤው መሪ ሀሳብ „ *እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ፡*“ የሚል ነበር። በዋና ተናጋሪነት ተጋብዘው የነበሩት የሰው ልጅ መብት ተከራካሪው፤ ጥቁር አሜሪካዊው ቄስ ማርቲን ሉተር ኪንግ ነበሩ። ነገር ግን በዚያው ዓ. ም. በዘረኞች ሰለተገደሉ በጉባኤው አልተገኙም። ከብዙዎች ተናጋሪዎች መካከል አንዱ የዛምብያ መሪ የነበሩት ኬነት ካውንዳ ነበሩ። እርሳቸውም „ የበለጸጉትና የደኸዩት ሀገሮች “ በሚል ርእስ ንግግር አድርገዋል።

፭ኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጉባኤ በ፲፱፻፷፰ ( እ.አ.አ.1976 ) ዓ. ም. በኅዳር ወር ናይሮቢ ውስጥ ተደረገ። በጉባኤው ከ፪፻፹፮ አብያተ ክርስቲያናት የተወከሉ ፯፻ ( 700 ) መልእክተኞች ተገኝተዋል። በዚህ ጉባኤ የተካሄደውን ሥርዓት ቅዳሴና ማኅሌት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መርታለች። በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለጉባኤው የመልካም ምኞት መግለጫ ልከዋል። የጉባኤው ዋና መሪ ሀሳብ „ *ኢየሱስ ክርስቶስ ነጻ ያወጣናል፤ አንድም ያደርገናል፡* “ የሚል ነበር። አንዳንድ የአፍሪካ ሀገሮች ገና ነጻ አልወጡም ነበርና ነው።

፮ኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጉባኤ በ፲፱፻፸፭ ( እ.አ.አ.1983 ) ዓ. ም. በነሐሴ ወር ቫንኩበር ውስጥ ተደርጓል። የማኅበሩ አባል ከሆኑ አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ ፰፻፵፯ (847 ) መልእክተኞች ተካፋዮች ሁነዋል። ሌሎችም የጉባኤው ተመልካቾች ተገኝተዋል። በዚህም

ጉባኤ ላይ የደቡብ አፍሪካው ሊቀ ጳጳስ፤ የኖቤል ተሸላሚው አቡነ ዲሞንድ ቱቱ „ *እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ያሸንፈናል* “ በሚል ርእስ ንግግር አድርገዋል። የጉባኤው መሪ ሀሳብ „ *ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ሕይወት ነው።*“ የሚል ነበር።

፯ኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጉባኤ በ፲፱፻፹፫ ( እ.አ.አ.1991 ) ዓ. ም. በየካቲት ወር በካምቤራ ተደረገ። ከ፫፻፲ አብያተ ክርስቲያናት የተላኩ ፰፻፶፪ ( 852 ) መልእክተኞች በጉባኤው ተካፍለዋል። ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ፳፫ መልእክተኞች ተገኝተዋል። የጉባኤው መሪ ሀሳብ „ *መንፈስ ቅዱስ ና፤ ፍጥረታትን ሁሉ አድስ።*“ የሚል ነበር። እስካሁን ከአንድ እስከ ስድስት በነበረው ጉባኤ ዋናው መሪ ሀሳብ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደነበር ልብ ብሎ ይመለከቷል።

፰ኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጉባኤ በ፲፱፻፺፩ ( እ.አ.አ.1998 ) ዓ. ም. በታኅሣሥ ወር በሐረሬ ከተማ ተካሄደ። ይህ ጉባኤ ከሌሎቹ ጉባኤዎች ሁሉ ለየት ያለ ነበር። ይህ አንጋፋ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የተመሠረተበትን የ፶ኛ ዓመት ኢዩቤልዩ ክብረ በዓሉን ያከበረው በዝባብዌ ዋና ከተማ በሐረሬ ነበር። በዚህ ጉባኤ ላይ ከ፫፻፴፱ አባላት አብያተ ክርስቲያናት የተወከሉ አንድ ሺህ መልክተኞች ተካፋዮች ሁነዋል። በአጠቃላይ ከተመልካቾች፤ ከክብር እንግዶችና ከጋዜጠኞች ጋር ከ፬ ሺህ ሕዝብ በላይ በጉባኤው ተገኝቷል። የጉባኤው ዋና መሪ ሀሳብም „ *ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ፤ በተስፋውም ደስተኞች ሁኑ።* “የሚል ነበር።

ከ፲፱፻፵- ፲፱፻፺፩፤ (1948-1998) በተደረጉት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጉባኤዎች ላይ ተለይተው የማያውቁት፤ ለብዙ ዓመታት የማኅበሩ ም/ቤት ዋና ጸሐፊ የነበሩት፤ የጃማይካው ተወላጅ ፊልጽ ፖተር በጉባኤው ላይ ተገኝተው ለ፶ ዓመታት የተካሄደውን የኅብረት ንቅናቄ በማውሳት ከፍተኛ አድናቆት የሚቸረው ንግግር አድርገዋል። ሌላው የክብር ተናጋሪ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚደንት የነበሩት ኔልሰን ማንዴላ ነበሩ። በንግግራቸውም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በደቡብ አፍሪካ የነበረው የዘር መድልዖ ተገርስሶ እስኪወድቅ ድርስ ላደረገው እርዳታ ከልብ አመስግነዋል። በተለይም በአጠቃላዩ ጉባኤ ፊት ቁመው ሲናገሩ „ *የናንተ ሚሲዮኖች ባይመጡ ኑሮ፤ እኔ ዛሬ ከፊታችሁ ባልቆምኩም ነበር።* “ ብለዋል። ሌላው ተናጋሪ የሀገሪቱ ፕሬዚደንት ሮበርት ሙጋቤ ነበሩ፡። እርሳቸውም የምዕራብ አገሮች ኅብረተ ሰብ ለሰዶማውያንና ለሰዶማውያት ያለው አስተያየት በስመ ዲሞክራሲ የተሸፈነ ሁኖ ስለአገኙት ከልብ አውግዘውታል። በጉባኤው የመነጋገሪያ መርሃ ግብር ተይዞለት ለውይይት እንዲቀርብ የምዕራብ ሀገሮች አብያተ ክርስቲያናት ተስማምተው ነብር። ነገር ግን የአሰተናጋጁ ሀገር ፕሬዚደንት ስለተቃወሙት ከውይይት መድረኩ እንዲሰረዝ ሁኗል። ፕሬዚደንት ሮበርት ሙጋቤ „*ግብረ ሰዶም የአፍሪካውያን ችግር አይደለም፤ አድራጊውም ከእንስሳ የባሰ ነው።*“ በማለት መላልሰው ኮንነውታል። ከዚህም የተነሣ የሆላንድ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች „ *የሰዶማውያን መብት*“ ተደፍሯል በማለትና የተቃውሞ ድምፅ በማሰማት፤ በ፰ኛው አጠቃላይ ጉባኤ ላይ ሳይገኙ ቀርተዋል። ከሰሜን አሜሪካና ከአውሮፓ የሄዱ ሰዶማውያንና ሰዶማውያት ደግሞ የተቃውሞ ሰልፍ አካሂደዋል። የአፍሪካ ተካፋዮች ግን ለፕሬዚደንት ሮበርት ሙጋቤ ያላቸውን አክብሮት ከገለጹ በኋላ „ *ታላቁ አፍሪካዊ መሪ* “ በማለት አወድሰዋቸዋል።

፰ኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ጉባኤ ለ፲፩ ቀናት በሐረሬ ከተማ ያካሄደውን አጠቃላይ ስብሰባ እንዳበቃ የሚከተለውን ቃለ መልእክት በመግለጫው አውጥቷል። *እስካሁን ቀጥሎ በኖረው ልዩነት የደረሰውን ኃዘን ተገንዝበናል። ሆኖም ሁልጊዜ እንደምናስታውሰው ከሚለያየን ይልቅ አንድ የሚያደርገን ይበዛል። በእኛ ልብ ሠርጾ የሚኖረው በክርስትና ሃይማኖት መለያየታችን ሳይሆን፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ልደት፤ ኑሮ፤ ሞትና ትንሣኤ የተገኘው ዘለዓለማዊ ሕይወት ነው። ስለዚህም ክርስቲያኖች እንደመሆናችን መጠን የሁላችን ልቡና ወደ እግዚአብሔር እንድንመለስ ያደርገናል። ስለዚህም በተስፋ ደስተኞች እንሆናለን። ወደ እግዚአብሔር ተመልሰን ፊት ለፊት የምንተያይ ከሆነ፤ ያን ጊዜ የምናየው የራሳችንን ፊት ይሆናል።* “ የሚል ነበር።

ይህን ከማናቸውም ጊዜ በተለየ መልክ የተካሄደውን ጉባኤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለማስተናገድ ጠይቃ ነበር። ነግር ግን ፬ሺህ ሕዝብ በአንድ ጊዜ ለማስተናገድ በቂ ቦታ ስለሌለ፤ ሐረሬም ከአዲስ አበባ የተሻለች ሁና በመገኘቷ፤ ይህን ከፍተኛ ዕድል ለማግኘት ችላለች። በቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በአዲስ አበባ ፬ ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ተካሂደዋል። በ፲፱፻፶፯ (እ.አ.አ 1965) ዓ. ም. ፫ቱ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ፓትርያርኮች በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድላይ ተገናኝተው በነገረ መለኮት፤ በክህነታዊ አግልግሎትና፤ በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ተነጋግረዋል፤ ውሳኔም አስተላልፈዋል። በ፲፱፻፷፫ (እ.አ.አ. 1971) ዓ. ም. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ማዕከላዊ ኮሚቴ ፤ በ፲፱፻፷፬ (እ.አ.አ.1972) ዓ. ም. የዓለም መጽሐፍ ቅዱስና የዓለም ወጣቶች ማኅበራት ስብሰባዎች ተካሂደዋል።

*ማጠቃለያ*

ለዓለም ክርስቲያኖች ከሚለያየን ይልቅ የሚያቀራርበን እንደሚበዛ የታወቀ ነው። ከዚህም በመነሣት ነው፤ በዘመናት መካከል የእርቅ፤ የሰላምና የኅብረት መንፈስ እንዲፈጠር ጥረት ሲደረግ የኖረው። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ም/ቤት ዋና መመሪያ ሁኖ የቀረበው፤ የሕዝብና የአሕዛብ ሐዋርያ የሆነው ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በላከው መልእክቱ በምዕራፍ ፬ ከቁጥር ፬-፮ እንዲህ ሲል የተናገረው ነው። „*በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ፤ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ። አንድ ጌታ፤ አንድ ሃይማኖት፤ አንዲት ጥምቀት፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን፤ በሁሉም የሚሠራ፤ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ፤ የሁሉም አባት አለ።* “ አንድ ተስፋ፤ አንድ መንፈስ፤ አንድ አካል፤ አንድ ጌታ፤ አንድ ሃይማኖት፤ አንዲት ጥምቀት፤ የሁሉም አባት የሆነ አንድ አምላክ አለ፤ በማለት ሐዋርያው ከአስተማረ፤ የክርስቶስ ምርጥ ዕቃና የቤተ ክርስቲያን ብርሃን ስለሆነ የዓለም ክርስቲያኖች ምንጊዜም መመሪያ አድርገው ሊቀበሉት ይገባል። ሌላ ክርስቶስ፤ ሌላ ጥምቀት፤ ሌላ ሃይማኖት፤ ልዩ መንግሥተ ሰማያት ያለ አስመስሎ የሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን ምእመናን መቀሰጥ ግን፤ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ሊወገዝ ይገባዋል። የዚህ ታላቅ ድርጅት አባል የሆኑ አብያተ ክርስቲያናትና ያልሆኑ ሁሉ ለዓለም ድኅነት ሲል የተወለደውን፤ በምድር ላይ የተመላለሰውን፤ የተሰቀለውንና የሞተውን፤ የተቀበረውንና በድል አድራጊነት የተነሣውን፤ በመጨረሻውም ቀን በግርማ መንግሥት ለመፍረድ የሚመጣውን ኢየሱስ ክርስቶስን በሰላምና በፍቅር፤ በኅብረትና በአንድነት ሊሰብኩት ይገባል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ „ *እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት።* “ ( ዮሐ.፲፭፤ ፲፪) ሲል አስተምሮናልና።

መርዓዊ ተበጀ